
ዓባይ ባንክ
Abay Bank

# ዓመታዊ ሪፖርት

## 2015 ዓ.ም

እ.ኤ.አ ሰኔ 30 ቀን 2023
ለተጠናቀቀው በጀት ዓመት



# በካርድዎ ግብይትዎን ያቀላጥፉ!

# BUY AND PAY WITH YOUR CARD!



ዓባይ - ታማኝ አገልጋይ!
**Abay : The Trustworthy Bank !**

# ማውጫ


የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ መልዕክት ...7

የባንኩ ዋና ሥራ አስፈፃሚ መልዕክት ...8

ባንኩ ያስመዘገባቸው አበይት ክንውኖች ...9

ክፍል1. የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት ...16

1.1. ኦፕሬሽናል ክንውኖች ...16

1.2. የገንዘብ-ነክ ክንውኖች ...18

1.3 ገንዘብ-ነክ ያልሆኑ ክንውኖች ...19

1.4 ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች ...20

ክፍል 2: የኦዲተሮች ሪፖርት ...22

2.1. የትርፍ ወይም ኪሳራ እና ሌሎች አጠቃላይ ገቢዎች መግለጫ ...26

2.2. የሀብትና የዕዳ ሂሳብ መግለጫ ...27

2.3 በአክሲዮን ማህበሩ ካፒታል ላይ የታየውን ለውጥ የሚያሳይ መግለጫ ...28

2.4 የጥሬ ገንዘብ ፍሰት መግለጫ ...29

## ራዕይ

ቀዳሚ ተመራጭ ባንክ መሆን!

## ተልዕኮ

የላቀ የባንክ አገልግሎት በመስጠት የባለድርሻ አካላትን ዕሴት ማሳደግ፣

## የባንኩ ዕሴቶች

- ደንበኛ ተኮርነት፣
- ተጠያቂነት፣
- በቡድን መስራት፣
- ሠራተኛ ተኮርነት፣
- ፈጠራ።

# የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት



ዶ/ር አምላኩ አስረስ

ቦርድ ሰብሳቢ



አቶ ታደሰ አሰፋ

ቦርድ ምክትል ሰብሳቢ



አቶ ቢያዝን እንኳሆነ

ዳይሬክተር



አቶ ሙላት ፀጋ

ዳይሬክተር



ወ/ሮ ማርታ አየነው

ዳይሬክተር



አቶ ጥበቡ አሉላ

ዳይሬክተር



አቶ ውቤ አጥናፉ

ዳይሬክተር



አቶ ደምስ ተሻገር

ዳይሬክተር



አቶ ነብዩ ስዩም

ዳይሬክተር

# የስራ አመራር አባላት



አቶ ዮኃላ ገሠሠ
ዋና ስራ አስፈፃሚ



አቶ አብርሃም አጆት
የብድር ዋና መኮንን



አቶ አሰፋ ተፈራ
የሪቴል ባንኪንግ ዋና መኮንን



አቶ በለጠ ቀኔ
የሰው ሀብት ዋና መኮንን



አቶ ወንድይፍራው ታደሠ
የስትራቴጂ ዋና መኮንን



አቶ ኤልያስ ብርሀኑ
የኢንፎርሜሽን ዋና መኮንን



አቶ ዳዊት አየነው
የውስጥ ኦዲት ዋና መኮንን



አቶ ፀጋ መኮንን
ሪስክ እና ኮምፕሊያንስ
ዋና መኮንን



ወ/ሮ ፅጌ አያሌው
ዓለም አቀፍ የባንክ አገልግሎት
ዋና መኮንን



አቶ ደሳለኝ አያሌው
ኮርፖሬት አገልግሎትዋና መኮንን



አቶ አንዳክመው ጌትነት
ዳይሬክተር - ህግ አገልግሎት



አቶ ዳንኤል ለገሠ
ዳይሬክተር - ስትራቴጂ እና የለውጥ
አስተዳደር

# የስራ አመራር አባላት



አቶ አቡበከር ናዚር

ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት ምክትል ዋና መኮንን



አቶ ሲሳይ ፀጋዬ

ባህር ዳር ዲስትሪክት ምክትል ዋና መኮንን



አቶ ሳሙኤል ተሾመ

ዳይሬክተር - የሰው ሀብት አስተዳደር



አቶ ማርቆስ ደመቀ

ዳይሬክተር - ሃብት ማሰባሰብ



አቶ አዮብ ንጉሴ

ዳይሬክተር - ግዢ እና ንብረት አስተዳደር



አቶ አበባው አበበ

ዳይሬክተር - የብድር ትንተና እና ግምገማ



አቶ ሰለሞን ተፈራ

ዳይሬክተር - ኮርፖሬት ብድር



አቶ ክርስቲያን ካሳ

ዳይሬክተር - ማርኬቲንግ



ወ/ሮ አመቤት ሰጦታው

ዳይሬክተር - ዓለም አቀፍ ቢዝነስ



አቶ ውብሸት አየናቸው

ዳይሬክተር - መሰረተ ልማት አስተዳደር



አቶ አንዱአለም ፋንቱ

ዳይሬክተር - አፕልኬሽን ማኔጅመንት



ወ/ሮ ፅጌሬዳ አዳም

ዳይሬክተር - አለም አቀፍ ንግድ

# የስራ አመራር አባላት



አቶ አንዱአለም ንጋቱ
ዳይሬክተር - የሰው ሀብት ልማት



አቶ ሙሉጌታ ቸኮል
ዳይሬክተር - ፖርትፎሊዮ አስተዳደርና ክሬዲት ኢንጌጅመንት



አቶ አብነት ማረው
ዳይሬክተር - አስኤምኢ እና ኮንሲዩመር ክሬዲት



አቶ ሲራክ ግርማ
ዳይሬክተር - ዲስትሪክት ድጋፍ



አቶ ስማእን አበበ
ሥራ አስኪያጅ - ሰሜን ምስራቅ ዲስትሪክት



አቶ ቢራራ ሰማኝ
ሥራ አስኪያጅ - ጎንደር ዲስትሪክት



አቶ ሂይሩ አብደላ
ሥራ አስኪያጅ - ድሬደዋ ዲስትሪክት



አቶ ዮናስ ተሰፋዬ
ሥራ አስኪያጅ - ደሴ ስትሪክት



አቶ ፋኑኤል ታዬ
ሥራ አስኪያጅ - ሃዋሳ ዲስትሪክት



አቶ ጥበቡ አንዳለ
ሥራ አስኪያጅ - ደቡብ ምዕራብ ዲስትሪክት



የአቶ ወርቅነህ ይርዳው
ዳይሬክተር - ፋይናንስ

አቶ ሁሴን
ሲኒየር ማኔጀር ባሀርዳር ዲስትሪክት

አቶ ሽባባው
ሲኒየር ማኔጀር ባሀርዳር ዲስትሪክት

አቶ ትዛዙ ወዳጆ
ዳይሬክተር ካምፓኒ ሴክሬተሪ

## የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ መልዕክት

### ውድ የባንካችን ባለአክሲዮኖች፣



የባንካችንን የ2015 ዓ.ም ዓመታዊ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ሳቀርብላችሁ ታላቅ ደስታ ይሰማኛል። ያለፈው ዓመት በርካታ ተግዳሮቶችና ዓለምአቀፍ ኢኮኖሚያዊ ቀውሶችን ያስተናገደ ዓመት ነበር።

መቋጫ የታጣለት የራሺያና ዩክሬይን ግጭት እንዲሁም ታይዋንን ማዕከል በማድረግ ተባብሶ የቀጠለው የቻይና እና የአሜሪካ ፍጥጫ እንዲሁም በበርካታ ሰብዓዊ ፍጡራን ላይ ጫና ያሳደረው የአየር ጠባይ ለውጥ፣ ጎርፍ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ የመሳሰሉ የተፈጥሮ አደጋዎች ዋነኛ መገለጫዎች ነበሩ። በሌላ በኩል ዓመቱ በፍላጐት እና አቅርቦት አለመጣጣም ምክንያት የተከሰተው ዓለም አቀፍ የዋጋ ንረት መሻሻል ያልታየበት ሆኖ አልፏል። ምንም እንኳን መንግስታት የኮቪድ-19ን ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ ለመቋቋም የተገበሩት የገንዘብ ፖሊሲ ማሻሻያ አቅርቦቱን የተገዳደረ ቢሆንም የአቅርቦት ሰንሰለቱ የራሺያ-ዩክሬን ግጭት እስከተከሰተበት ወቅት ድረስ ወደ ቅድመ ኮቪድ-19 ደረጃው በመመለስ መሻሻል ያሳየ ሁነት ነበር።

በዓመቱ ውስጥ እነዚህን የመሳሰሉ ተግዳሮቶችና ተፅዕኖዎች የታዩ ቢሆንም የዓለም ጤና ድርጅት ዓለማችን ከወረርሽኙ ዳፋ እየተላቀቀች መሆኑን መግለጹ እንደመልካም አመላካች የሚታይ ነው። በሌላ በኩል ቻይና እና ብራዚል በየራሳቸው የመገበያያ ገንዘብ የንግድ ልውውጥ ለማካሄድ ስምምነት ላይ መድረሳቸው በዓመቱ ከተከሰቱ አበይት ጉዳዮች መካከል ሊጠቀስ የሚችል ነው።

አ.ኤ.አ. የ2022 የተመዘገበው የ3.5 በመቶ ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ዕድገት ከቀደሙት ዓመታት አማካይ ዝቅ ያለ ከመሆኑ በተጨማሪ የኢኮኖሚ ዕድገት ትንበያው እ.ኤ.አ. በ 2023 ወደ 3 በመቶ እንደሚያሽቆለቁል አመላክቷል። ከግጭቶች፣ ከሸቀጦች ዋጋ ንረት፣ ከአየር ንብረት ለውጥ እንዲሁም ከውጭ ዕዳ ሸክም ጋር የሚታገሉት የአፍሪካ ሀገሮችም ተመሳሳይ ተግዳሮቶችን ተጋፍጠዋል።

ሀገራችን ኢትዮጵያ ሁለት ዓመት ካስቆጠረው የሰሜኑ ግጭት ወጥታ ሰላምና መረጋጋት ላይ ትገኛለች። በመሆኑም የኢኮኖሚ ዕድገቱ ከባለፈው ዓመት የ6.4 በመቶ ምጣኔ አንፃር መሻሻልን አሳይቶ የ7.5 በመቶ ዕድገት አስመዝግቧል።

በአንጻሩ ባንካችን እነዚህን ሁሉ ተግዳሮቶች ተቋቁሞ አመርቂ ውጤት አስመዝግቧል። በዚህም መሰረት ጠቅላላ የተቀማጭ ገንዘብ የ29 በመቶ ዓመታዊ ዕድገት በማስመዝገብ ብር 41.8 ቢሊዮን ደርሷል።

የደንበኞቹን ቁጥርም የ49 በመቶ ዓመታዊ ዕድገት በማሳየት በዓመቱ መጨረሻ ላይ 2.5 ሚሊዮን ያደረሰ ሲሆን የአገልግሎት ተደራሽነቱን በማስፋት በበጀት ዓመቱ 110 አዳዲስ ቅርንጫፎችን ከፍቷል። ትርፋማነቱን ብር 2.1 ቢሊዮን በማድረስ ባንኩን ወደ አዲስ ከፍታ መውሰድ ተችሏል።

በቀጣይም ለተሻለ ዕድገትና ለዘላቂ ውጤታማነት የሚያበቃ አዲስ መሪ ዕቅድ በማዘጋጀት ረገድ ሰፊ ተቋማዊ እንቅስቃሴ ተደርጓል። በዚህ መሰረት "ጉዞ ከፍታ" በሚል ስያሜ ከ2016 እስከ 2021 ድረስ ሥራ ላይ የሚውል አዲስ የአምስት ዓመት መሪ ዕቅድ ተዘጋጅቷል። ከዚህም ጋር ተያይዞ ባንካችን "ቀዳሚ ተመራጭ ባንክ መሆን" የሚል ራዕይ ሰንቆ "የላቀ የባንክ አገልግሎት በመስጠት የባለድርሻ አካላትን ዕሴት የማሳደግ" ተልዕኮ በማንገብ ጉዞውን ጀምሯል።

ይህን ተከትሎም አዲስ የመዋቅር ጥናት የተተገበረ ሲሆን የባንካችንን ብራንድ መገለጫዎች የማሻሻል ወሳኝ ፕሮጀክትም በሂደት ላይ ይገኛል።

በቀጣይም በተግዳሮቶች ሳንገታ ለስቀመጥናቸው ግቦች መሳካት ጠንክረን በመሥራት በሙያዊ ጥረት እና በሙሉ ትኩረት በመንቀሳቀስ የሚገጥሙንን መሰናክሎች ማለፍ እንደምንችል ሙሉ እምነት አለኝ።

በመጨረሻም የሥራ ጊዜያቸውን በስኬት በማጠናቀቅ ለተሰናበቱ እንዲሁም ለተረካቢው የቦርድ አባለት ላበረከቱት የላቀ የአመራር እና ክትትል አስተዋጽኦ ከልብ ማመስገን እወዳለሁ። ለሥራ አመራር አባላትና ለታታሪ ሠራተኞቻችን በሙሉ እንዲሁም ሁሌም ከጐናችን ላሉት ውድ ደንበኞቻችን አድናቆቴን ከምስጋና ጋር መግለጽ እወዳለሁ። በስራችን ሁሉ ለተባበሩን የመንግስት ተቋማት እንዲሁም ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የፋይናንስ ዘርፉን የተረጋጋ በማድረግ ረገድ ለነበራቸው ወሳኝ ሚና በተለየ መልኩ ማመስገን እወዳለሁ።

አመሰግናለሁ!



አምላኩ አስረስ (ዶ/ር)
የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ

## የዋና ስራ አስፈጻሚ መልዕክት

ውድ የባንካችን ባለአክሲዮኖች፣



ያለፈውን የበጀት ዓመት የባንካችን የሥራ አፈፃፀም ለመገምገም በድጋሚ በመገኛኘታችን የተሰማኝን ደስታ ለመግለጽ እወዳለሁ፡፡ የ2015 ዓ.ም ከዓለም አቀፍ መድረክ አንስቶ እስከ ሀገራዊ ከባቢዎች ድረስ እንደምታ በነበራቸው ተግዳሮቶች የታጀበና በበርካታ አሉታዊ ሁነቶች የሚጠቀስ ዓመት ሆኖ አልፏል፡፡ ባለፈው ዓመት የተቀሰቀሰው የራሺያ-ዩክሬን ግጭትም በዚህም ዓመት ያልተቋጨ አጀንዳ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ከአየር ጠባይ ለውጥ ጋር ተያይዞ ዓለማችን አስከፊ የተፈጥሮአዊ ቀውሶችን እና አደጋዎችን ስታስተናግድ ቆይታለች፡፡

የዋጋ ንረቱ ከፍላጐት እና አቅርቦት አለመመጣጠን ጋር ተያይዞ በአጠቃላይ ከፍ ብሎ የቆየ ቢሆንም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መምጣቱ ተስተውሏል፡፡ የዓለምአቀፉ የገንዘብ ተቋም /IMF/ ሪፖርት እንደሚያሳየው የዓለም የኢኮኖሚ እድገት እ.ኤ.አ. በ2022 ደካማ የነበረ ሲሆን የ3.5 በመቶ የዕድገት ምጣኔ አስመዝግቧል፡፡ እ.ኤ.አ. የ2023 ትንበያዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ ቅናሽ እያሳዩ ሲሆን የቅርብ ጊዜው ግምት የ3 በመቶ ምጣኔን ያመለክታል፡፡

በአፍሪካም የተስተዋሉት የዕድገት ተግዳሮቶች በዓለምአቀፍ ደረጃ ከታዩት የተለዩ አልነበሩም፡፡ በርካታ ሀገራት በተለያዩ ቀውሶች ሲናጡ ቆይተዋል፡፡ በዋነኛነትም የራሺያ- ዩክሬን ግጭት፣ የሸቀጦች ዋጋ መናርና የምግብ እጥረት፣ አስከፊ የአየር ንብረት ለውጥ አደጋዎች እና የዕዳ ጫናዎችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ በተለይ ከሰሀራ በታች ባሉ ሀገራት ጠቅላላ ምርት የዛሬ ዓመት ከተመዘገበው የ4.1 በመቶ የዕድገት ምጣኔ ወደ 3.6 በመቶ ዝቅ ሊል ችሏል፡፡ እ.ኤ.አ. የመጪው 2023 ትንበያም ተጨማሪ ቅናሽ እንደሚያስመዘግብና ወደ 3.1 በመቶ እንደሚወርድ ይጠበቃል፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ በአፍሪካ ህብረት ሸምጋይነት የተካሄደውን ስምምነት ተከትሎ ከሁለት ዓመት የሰሜኑ ግጭት በኋላ ወደ ሰላማዊ ጉዞ ተመልሳለች፡፡ ምንም እንኳን የበጀት ዓመቱ በተግዳሮቶች የታጀበ ቢሆንም ኢኮኖሚው እምና ካስመዘገበው የ6.4 በመቶ ዕድገት ወደ የ 7.5 በመቶ ከፍ ማለቱን መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በሶስቱ ዋና ዋና የኢኮኖሚው ዘርፎች የታየውን እንቅስቃሴም ስንመለከት በኢንዱስትሪ እና የግብርና ዘርፎች ከታየው አነስተኛ ቅናሽ አንጻር በአገልግሎት ዘርፍ መጠነኛ ጭማሪ ተመዝግቧል፡፡

የባንክ ኢንዱስትሪው የመንግስት ባንኮችን ጨምሮ የተሳታፊዎቹን ብዛት 29 በማድረስ ሰፊ የውድድር መድረክ ሆኗል፡፡ በዓለምአቀፍ እንዲሁም በሀገር ውስጥ የተከሰቱ መጠነ-ሰፊ ችግሮችን በመቋቋም ዘርፉ በሁሉም ዋና ዋና መመዘኛዎች ማለትም እንደ ተቀማጭ ገንዘብ፣ ካፒታል፣ የአገልግሎት ተደራሽነት፣ እንዲሁም ትርፍ አንፃር ዕድገት ማስመዝገቡን ማስቀጠል ችሏል፡፡

ባንካችን ዓባይ ከሁሉም አበይት መመዘኛዎች አንጻር አበረታች ዕድገት አስመዝግቧል፡፡ የተቀማጭ ገንዘብ መጠን የ29 በመቶ ዓመታዊ ዕድገት በማስመዝገብ ብር 41.8 ቢሊዮን ደርሷል፡፡ አዳዲስ ደንበኞችን ከማፍራት አኳያ የደንበኞቻችን ቁጥር የ49 በመቶ ዓመታዊ ዕመርታ በማሳየት 2.5 ሚሊዮን በማድረስ አመርቂ ውጤት አስመዝግቧል፡፡

አዳዲስ አካባቢዎችንም በማሰስ በመላ ሀገሪቱ በአጠቃላይ 110 አዳዲስ ቅርንጫፎች የተከፈቱ ሲሆን ይህም ከባንኩ ምስረታ አንስቶ ከፍተኛው ዓመታዊ ዕድገት ነው፡፡

ገቢን ከማሳደግ እና ወጪዎቻችንን ከመቆጣጠር አንፃር ያከናወናቸው አጠቃላይ የውጤታማነት አድማስን የማስፋት ሥራ አዲስ የትርፋማነት ከፍታ እንድናስመዘግብ አስችሎናል፡፡ በዚሁም መሠረት ጠቅላላ ትርፋችን ከታክስ በፊት ብር 2.1 ቢሊዮን የደረሰ ሲሆን ከባለፈው ዓመት አንጻር ሲታይ የ63 በመቶ ዓመታዊ ዕድገት የታየበት ነው፡፡ ባንካችን ተገቢውን የብድር ሂደቶች እና ዲሲፕሊን የተከተሉ አሠራሮችን ከመተግበሩ ጋር ተያይዞ በዓመቱ ውስጥ የተመዘገበው የታማሚ ብድር ምጣኔ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ዝቅተኛ ምጣኔ አንጻር በጥሩ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ የባንካችንንም ዕሴቶች እንዲሁም ተልዕኮ በሚያንጸባርቅ መልኩም ባንካችን ለተለያዩ ማኅበረሰቦች በርካታ ድጋፍ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ ባንካችን ለበርካታ ወገኖች ለጋስ እጆቹን በመዘርጋት እስከ ብር 34.6 ሚሊዮን የሚደርስ ገንዘብ ለግሷል፡፡

ባሳለፍነው ዓመት በባንካችን ከተከናወኑ ዓበይት ጉዳዮች መካከል "ጉዞ ከፍታ" የተሰኘው የአምስት ዓመት የመሪ ዕቅድ ዝግጅት ይገኝበታል፡፡ አዲሱ መሪ ዕቅድ በውጭ አማካሪ በታገዘ በባንኩ የውስጥ ዓቅም የተዘጋጀ ሲሆን ከ2016 እስከ 2021ዓ.ም. ድረስ የምንንቀሳቀሰበት ይሆናል፡፡ ይህንንም ወሳኝ ሥራ ተከትሎ ባንካችን የመሪ ዕቅዱ የቅድመ-ትግበራ ሙሉ ዝግጅቱን አጠናቋል፡፡ በዚሁም መሠረት የሥራ ሂደቶችን በማሻሻልና አመርታ በማምጣት መሪ ዕቅዱን በበቂ ሁኔታ መደገፍ የሚያስችል አዲስ የመዋቅር ጥናት በማካሄድ ወደ ስራ የገባ ሲሆን ይህንንም ተከትሎ የሰው ኃይል ምደባ ተጠናቅቋል፡፡ የባንካችንን ብራንድ ጉልህነት እንዲሁም አጠቃላይ ዕይታ የማሻሻል /ሪብራንዲንግ/ ሥራም ተጀምሯል፡፡

በቀጣይም በፈታኝ ሁኔታዎች ውስጥ በመጓዝና ተግዳሮቶች በመቋቋም ለግቦቻችን ስኬት በጽናት በመስራት ለተሻለ ውጤታማነት እንተጋለን፡፡ አዲሱን ዓመትም ከተለምናቸው ግቦች የላቀ ውጤት ለማስመዝገብ የምንጥርበት ዓመት ይሆናል፡፡

በዚህ ዓመት ለተመዘገበው ውጤት ከጐናችን ለነበሩት ባለድርሻ አካላት ሁሉ ምስጋና ማቅረብ እወዳለሁ፡፡ ከሁሉ አስቀድሜ ጠንካራ የስራ መነሳሳት ላሰረጹብን የባንካችን የዲሬክተሮች ቦርድ አባላት እንዲሁም የስራ ጊዜያቸውን ፈጽመው በክብር ለተሰናበቱ የቀድሞው ቦርድ አባላት ላበረከቱት አስተዋጽኦ እና አገዛ ላቅ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ በተጨማሪም የባንካችን የሥራ አመራር አባላትና ሰራተኞች ላሳዩት ትጋትና ታታሪነት እንዲሁም ጥብቅ በሆነ የአብሮነት ጉዞ ከባንካችን ጋር ለተቆራኙት ውድ ደንበኞቻችንና ባለአክሲዮኖች የከበረ ምስጋናየን እያቀረብኩ ዘወትር በተሻሻሉ አገልግሎቶቻችን ደንበኞቻችንን ለማርካት ቃል በመግባት ጭምር ነው፡፡ በመጨረሻም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የፋይናንስ ዘርፉን ጤንነት ከማስጠበቅና ባንኩን ከመደገፍ አንጻር ላደረገልን አስተዋጽኦ ልባዊ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡


አመሰግናለሁ!





የኋላ ገሠሠ
ዋና ስራ አስፈጻሚ

## የዓበይት ክንውኖች አጭር መግለጫ























ዓባይ ባንክ
Abay Bank

# ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት

# INTEREST FREE BANKING SERVICES



## SADiiQ صديق

ዓባይ - ታማኝ አገልጋይ !
**Abay : The Trustworthy Bank !**




## ከሳፋሪኮም ኢትዮጵያ ጋር የተደረገ የስራ ስምምነት








# የ2015 ዓ.ም በጀት ዓመት የከፍተኛ ግብር ከፋይ ተሸላሚ






# የፋይናንስ ድጋፍ ከተደረገባቸው ፕሮጀክቶች መካከል



ዓባይ ባንክ
Abay Bank

# ንግሥት የቁጠባ ሂሳብ
# NIGIST SAVING PRODUCT




ዓባይ - ታማኝ አገልጋይ!
**Abay : The Trustworthy Bank !**

# ክፍል 1
## የኦዲተሮች ሪፖርት

# ክፍል1. የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት

እ.ኤ.አ. ሰኔ 30 ቀን 2023 ዓ.ም የተጠናቀቀውን የባንኩን ዓመታዊ የስራ ክንውን እና የኦዲተሮች ዝርዝር ሪፖርት እንደሚከተለው ሲያቀርብ የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ከፍተኛ ደስታ ይሰማዋል፡፡ በሪፖርቱ የመጀመሪያ ክፍል የባንኩ ዓመታዊ አፈጻጸም በአጭሩ የሚቀርብ ሲሆን በክፍል ሁለት ላይ ጠቅለል ያለ የኦዲተሮች ሪፖርት ተካትቶ ቀርቧል፡፡

## 1.1. ኦፕሬሽናል ክንውኖች


### 1.1.1. የተቀማጭ ገንዘብ ክንውን

በተጠናቀቀው ዓመት ባንኩ ካስመዘገባቸው አመርቂ ውጤቶች መካከል የተቀማጭ ሂሳብ አፈጻጸም አንዱ ሲሆን በዓመቱ ውስጥ ተጨማሪ 9.4 ቢሊዮን ብር በመሰብሰብ የባንኩ አጠቃላይ የመደበኛ እና ከአባይ ሳዲቅ ከወለድ ነጻ ተቀማጭ ሂሳብ ብር 41.8 ቢሊዮን ደርሷል፡፡ ይህም ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የ29 በመቶ ዕድገት የተመዘገበበት ነው፡፡ ከተሰበሰበው አጠቃላይ ተቀማጭ ገንዘብ ውስጥ በመደበኛው የቁጠባ ሂሳብ የተሰበሰበው ተቀማጭ ከቀዳሚው ዓመት የ 28 በመቶ ዕድገት በማሳየት ብር 39.5 ቢሊዮን ማድረስ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይም ከወለድ ነጻ አገልግሎት ደንበኞች የቆጠቡት ገንዘብ መጠን ብር 2.3 ቢሊዮን የደረሰ ሲሆን ዓመታዊ ዕድገቱም 40 በመቶ ደርሷል፡፡


በዓመቱ ውስጥ ከተሰበሰበው አጠቃላይ ተቀማጭ መካከል የቁጠባ ተቀማጭ ገንዘብ መጠን ብር 25.5 ቢሊዮን የደረሰ ሲሆን ከቀዳሚው ዓመት የ18 በመቶ ዕድገት አሳይቷል፡፡ በሌላ በኩል የተንቀሳቃሽ ሂሳብ የ42 በመቶ ዓመታዊ ዕድገት በማስመዝገብ አጠቃላይ ተቀማጭ ብር 12.9 ቢሊዮን ደርሷል፡፡ በአንጻሩ የጊዜ ገደብ ተቀማጭ ሂሳብ ካለፈው ዓመት የ90 በመቶ ዕድገት በማስመዝገብ አጠቃላይ መጠኑ ወደ ብር 3.4 ቢሊዮን ከፍ ብሏል፡፡

በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት ከ817,573 በላይ አዳዲስ ደንበኞችን በማፍራት የባንኩን የመደበኛና የአባይ ሳዲቅ ከወለድ ነጻ አስቀማጭ ደንበኞች ቁጥር 2.5 ሚሊዮን ማድረስ ተችሏል፡፡ ይህም በዓመቱ የ49 በመቶ ጭማሪ የተመዘገበበት ሲሆን የደንበኞቻችን ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ ማደግ ለተቀማጭ ገንዘቡ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከተ አንደኛው ምክንያት ነው፡፡

ምስል 1: የተቀማጭ ገንዘብ ንጽጽር በዓይነት




ባለፉት ዓመታት የባንኩ የተቀማጭ ሒሳቦች ድርሻ መጠነኛ ለውጥ በማስመዝገብ ዋነኞቹ የቁጠባ የተንቀሳቃሽ እና የጊዜ ገደብ የተቀማጭ ሂሳቦች ድርሻ እንደ የቅደም ተከተላቸው የ61 በመቶ የ31 በመቶ እና የ 8 በመቶ ድርሻ ይዘዋል፡፡




ምስል 2. የተቀማጭ ገንዘብ በዓይነት ድርሻ


### 1.1.2. የብድር አገልግሎት

በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት ባንኩ በተለያዩ ዘርፎች ለተሰማሩ ደንበኞቹ የፋይናንስ አቅርቦቱን አጠናክሮ የቀጠለ ሲሆን ለመደበኛውም ሆነ ለአባይ ሳዲቅ አገልግሎት ተጠቃሚ ደንበኞች ያቀረበው የብድር መጠን ዓመታዊ የ37 በመቶ ዕድገት በማስመዝገብ ብር 37 ቢሊዮን ማድረስ ችሏል፡፡

ባንኩ በሁሉም የኢኮኖሚ ዘርፎች መካከል ያለውን የብድር ስርጭት ሚዛናዊ ለማድረግ ያስቀመጠውን አቅጣጫ ለማሳካት ያደረገው ጥረት ለየዘርፎቹ ያቀረበው የብድር መጠን አመታዊ ዕድገት እንዲያስመዘግብ አስችሎታል፡፡ ዓባይ ባንክ ካቀረበው የብድር መጠን ውስጥ ዓለም ዓቀፍ ንግድ ዘርፍ ላይ ለተሰማሩ ደንበኞች ያቀረበው የብድር መጠን ከአጠቃላዩ የ38.8 በመቶ ድርሻ በመያዝ ቀዳሚ ሲሆን ይህም ለዘርፉ የተሰጠውን ሀገራዊ አቅጣጫ የተከተለ ነው፡፡ ባንኩ ለሃገር ውስጥ ንግድና አገልግሎት ያቀረበው የብድር መጠን በ17.9 በመቶ ድርሻ የሚከተል ሲሆን ለኮንስትራክሽን ዘርፍ የቀረበው ብድር የ14.3 በመቶ ይይዛል፡፡ የማምረቻ ዘርፍ የ10.6 በመቶ እና የትራንስፖርት እና ኮሚዩኒኬሽን እና ሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች እንደየቅደም ተከተላቸው 6.6 በመቶ እና የ11.8 በመቶ ድርሻ ወስደዋል፡፡

በሌላ በኩል ባንኩ ከወለድ ነጻ ተጠቃሚ ለሆኑ ደንበኞቹ ያቀረበው የፋይናንስ መጠን ብር 1.5 ቢሊዮን የደረሰ ሲሆን ይህም የ106 በመቶ ዓመታዊ ዕድገት የታየበት ነው፡፡

ምስል 3፡-የብድር ስብጥር በኢኮኖሚ ዘርፎች (በሚሊዮን ብር)




ማስታወሻ፡-ለሆቴልና ቱሪዝም፣ለግብርና እና ለሰራተኞች የተሰጡ ብድሮች ሌሎች በሚል ተጠቃለዋል













በባንኩ ፋይናንስ የተደረጉ ፕሮጀክቶች

## 1.1.3. የዓለምአቀፍ ባንክ አገልግሎት


በሀገራችን ላይ ከተከሰተዉ የፖለቲካ እና የጸጥታ ተግዳሮት ጋር ተያይዞ የሃገሪቱ የወጪ ንግድ ፈተና የገጠመው ቢሆንም ባንካችን ችግሮችን በመቋቋም በሁሉም የውጭ ምንዛሪ ምንጮቻችን በኩል ያመነጨው አጠቃላይ የውጭ ምንዛሪ መጠን የ31 በመቶ ዓመታዊ ዕድገት አስመዝግቧል፡፡ ባንኩ በዓመቱ ከሰበሰበው የውጭ ምንዛሪ ውስጥ የ63 በመቶ ድርሻ በመያዝ ከወጪ ንግድ ምንጭ የተገኘው የውጭ ምንዛሪ መጠን ቀዳሚው ሲሆን ይህም የ14 በመቶ ዓመታዊ ዕድገት ያሳየ ነው፡፡ በተመሳሳይም ከስዊፍት እና ከገንዘብ ዝውውር ምንጮቻችን በኩል የተገኘው የውጭ ምንዛሪ ከቀዳሚው ዓመት አንጻር ዕድገት የተመዘገበበት ቢሆንም በአንጻሩ ከጥሬ ገንዘብ ምንዛሪ እና ከብሔራዊ ባንክ ግዢ የሚጠበቀው የውጭ ምንዛሪ መጠን ዓመታዊ ቅናሽ አሳይቷል፡፡

ባንካችን የውጭ ምንዛሪ ግኝቱን ለማሳደግ የሚረዱ በርካታ ጥረቶች ያከናወነ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ለስድስት ተከታታይ አመታት ለውጭ ምንዛሪ አስገኚ ደንበኞቹ ያቀረበው የሽልማት ማበረታቻ፤ ከተጨማሪ የገንዘብ አስተላላፊ ድርጅቶች እና በዓለምአቀፍ ደረጃ ከሚሰሩ የወጭ ንግድ ግንኙነት አጋሮቻችን ጋር በጥምረት ለመስራት ያደረጋቸው ጥረቶች ሁነኛ ተጠቃሾች ናቸው፡፡

## 1.2. ገንዘብ-ነክ ክንውኖች

### 1.2.1. ገቢ

ባንኩ በዓመቱ ውስጥ የብር 7.1 ቢሊዮን ገቢ በመሰብሰብ ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ጊዜ የ61 በመቶ ዕድገት ማስመዝገብ ችሏል፡፡ ከተሰበሰበው አጠቃላይ ገቢ ውስጥ ከወለድ የተገኘ ገቢ የ78 በመቶ ድርሻ የነበረው ሲሆን ቀሪው 22 በመቶ ደግሞ ከኮሚሽን እና አገልግሎት እንዲሁም ከሌሎች የገቢ ምንጮች የተገኘ ገቢ ነው፡፡





የገቢ ስብጥር

### 1.2.2. ወጪ


ካለፈው ዓመት የ59 በመቶ ጭማሪ ያስመዘገበው የባንኩ ዓመታዊ ወጪ ብር 4.9 ቢሊዮን ደርሷል፡፡ በዓመቱ ከተመዘገበው አጠቃላይ ወጪ ባንኩ ከወለድ ውጭ ለሆኑ የወጪ ምክንያቶች ያወጣው ወጪ የ 68 በመቶ ድርሻ ያለው ሲሆን ለወለድ ክፍያ የዋለው ወጪ ቀሪውን የ 32 በመቶ ድርሻ ይወስዳል፡፡

ከወለድ ውጭ ካሉ ወጭዎች ለደመወዝና ጥቅማ ጥቅሞች ክፍያ ያዋለው ወጪ በ58.3 በመቶ በመሆን ከፍተኛውን ድርሻ ሲይዝ ተከታዩን ደረጃ የአስተዳደራዊ ወጪዎች በ22.4 በመቶ ይይዛል፡፡ ቀሪው 19.3 በመቶ ለተበላሹ ብድሮች መጠባበቂያ፣ ለእርጅና ቅናሽ እና የሌሎች ወጪዎች ድርሻ ነው፡፡




### 1.2.5 ትርፍ

በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት ባንኩ የትርፍ መጠኑን ከግብር በፊት ብር 2.1 ቢሊዮን አድርሷል፡፡ ይህም ከቀዳሚው ዓመት ጋር ሲነጻጸር የብር 823 ሚሊዮን ወይም የ63 በመቶ ጭማሪ የተመዘገበበት ነው፡፡




### 1.2.3. ጠቅለላ ሀብት

እ.ኤ.አ ሰኔ 30 ቀን 2023 ዓ.ም. የተመዘገበው የባንኩ አጠቃላይ ሃብት ብር 55 ቢሊዮን ደርሷል፡፡ የባንኩ አጠቃላይ ሃብት የ35 በመቶ ዓመታዊ ዕድገት ያሳየ ሲሆን በዓመቱ ውስጥ ባንኩ ያቀረበው የብድር መጠን ዕድገት፣ የሀብት ማሰባሰብ ጥረት እና የሌሎች ቋሚ ሀብቶች ዕድገት ለባንኩ አጠቃላይ የሃብት ዕድገት የላቀ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡

### 1.2.4. ካፒታል

እ.ኤ.አ ሰኔ 30 ቀን 2023 ዓ.ም. የተመዘገበው የባንኩ አጠቃላይ ሃብት ብር 55 ቢሊዮን ደርሷል፡፡ የባንኩ አጠቃላይ ሃብት የ35 በመቶ ዓመታዊ ዕድገት ያሳየ ሲሆን በዓመቱ ውስጥ ባንኩ ያቀረበው የብድር መጠን ዕድገት፣ የሐብት ማሰባሰብ ጥረት እና የሌሎች ቋሚ ሀብቶች ዕድገት ለባንኩ አጠቃላይ የሃብት ዕድገት የላቀ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡

## 1.3 ገንዘብ-ነክ ያልሆኑ ክንውኖች

### 1.3.1 ቅርንጫፍ ማስፋፋት

በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት አገልግሎት መስጠት የጀመሩትን 110 አዳዲስ ቅርንጫፎችን ጨምሮ የባንኩን ተደራሽነት በማስፋት አጠቃላይ የቅርንጫፍ ስርጭቱን 483 ማድረስ ተችሏል፡፡ ይህ ፈጣን የቅርንጫፎች ዕድገት አዳዲስ የገበያ ዕድሎችንና አካባቢዎችን ተደራሽ መሆንን ታሳቢ ያደረገ እንቅስቃሴ ነው፡፡ በሂደቱም ከወለድ ነጻ የሆነ የዓባይ ሳዲቅ አገልግሎት ብቻ የሚሰጥባቸው ተጨማሪ ቅርንጫፎች በመክፈት 20 ማድረስ የተቻለ ሲሆን ይህንኑ ከወለድ ነጻ አገልግሎት የሚሰጡ መስኮቶችን በማስፋፋት አገልግሎቱን በ395 ቅርንጫፎቻችን በኩል በመሰጠት ላይ እንገኛለን፡፡

### 1.3.2 የሰው ኃይል

ከባንኩ ፈጣን ዕድገት ጋር የሚመጣጠን ብቁ እና ተወዳዳሪ የሰው ኃይል ቅጥር በማከናወን ውጤታማ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ዝግጁነት ለመፍጠር በተደረገው ጥረት ባንኩ ለ1,636 አዳዲስ አመልካቾች የስራ ዕድል ፈጥሯል፡፡ ይህም ባንኩ በቋሚነት ቀጥሮ የሚያስተዳድራቸውን እና በቀጣሪ ድርጅቶች በኩል የሚተዳደሩ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን ቁጥር የ23 በመቶ ዓመታዊ ዕድገት በማስመዝገብ አጠቃላይ የባንኩ ሰራተኞችን ቁጥር 8,626 አድርሶታል፡፡ ከባንኩ ቋሚ ሰራተኞች መካከል 98 በመቶው በተለያዩ ሙያዎች ቢያንስ በመጀመሪያ ዲግሪ የተመረቁ ናቸው፡፡

ከባንኩ አጠቃላይ የሰው ኃይል ውስጥ 4,328 በቀጣሪ ድርጅቶች በኩል የሚተዳደሩ ሲሆን ቀሪዎቹ 4,298 ሰራተኞች ባንኩ በቋሚነት ቀጥሮ የሚያሰራቸው ናቸው፡፡ የሰራተኞቹን ብቃትና ክህሎት ከማሳደግ አንጻር ባንኩ ቀጣይነት ያለው የሰው ኃይል ልማት ስርዓት በመዘርጋት የተለያዩ ስልጠናዎችን በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ በዚህ መሰረት ለ5,256 ቋሚ ሰራተኞች በጥናት በተለዩ መሻሻል የሚያስፈልጋቸው ዘርፎችና በተለያዩ የስልጠና መስኮች ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት የሚያስችሉ ስልጠናዎችን ለመስጠት ጥረት ተደርጓል፡፡

ባንኩ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የሚመራበትን መሪ ዕቅድ ማዘጋጀቱን ተከትሎ ለዕቅዱ ማስፈጸሚያ የሚሆን አጠቃላይ የመዋቅር ማስተካከያ ጥናት በማከናወን ተግባራዊ አድርጓል፡፡ ይህን ተከትሎም ተያያዥ የስራ መደብ እና የሰራተኞች ደመወዝና ጥቅማጥቅም ማሻሻያ ማዕቀፍ በማዘጋጀትና ወደ ስራ በማስገባት የባንኩን ውጤታማነት የሚያሻሽሉ፣ የሰራተኛውን ተነሳሽነት የሚጨምሩና ለስትራቴጅክ ዕቅዱ መሳካት ከፍተኛ ሚና የሚኖረውን መደላደል ለመፍጠር የሚያስችል ተግባር ተከናውኗል፡፡

### 1.3.3 የዲጂታል ባንኪንግ አገልግሎት

የምንገኝበት ወቅት የተጠናከረ የዲጂታል ቴክኖሎጂዎች አቅም የባንክ አገልግሎቶችን ማቅረቢያና ቁልፍ የመወዳደሪያ ምክንያቶች እየሆኑ መምጣታቸውን እንገነዘባለን፡፡ ዓለምአቀፍ የባንኪንግ ልምዶችም የሚያመለክቱት ትልቁን የገበያ ድርሻ በመያዝ መሪ የሆኑት ባንኮች በዲጂታል ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ከተወዳዳሪዎቻቸው ቀዳሚ መሆናቸውን ነው፡፡ ስለሆነም ባንኮች የዲጂታል አቅሞቻቸውን በማጠናከር፣ የዲጂታል ባንኪንግ አገልግሎቶችን ለማበልጸግ፣ ለመምራት እና ለማስፈጸም የሚያስችል የሰው ኃይል ብቃትን ከማረጋገጥ በተጨማሪ የደንበኞችንም ሆነ የባንኩን የመረጃ ሀብት ከጥቃት ለመከላከል የሚያስችል የተቀናጀ ስርዓት መዘርጋት የባንኮች ቀዳሚ ተግባር መሆኑ እሙን ነው፡፡

ይህን እውነት ከግምት ውስጥ በማስገባት ባንኩ የዲጂታል አቅሞቹን ለማጠናከር እንዲያስችለው ለዘርፉ ከፍተኛ መዋዕለ-ነዋይ ፈሰስ ማድረጉን ቀጥሎበታል፡፡ በመሆኑም በተጠናቀቀው ዓመት ለሞባይል ባንኪንግ ሞጁል ተከታታይ ማጠናከሪያ ስራዎች፣ ለተለያዩ ሲስተሞች አገልግሎት የሚውሉ የተጨማሪ ሰርቨሮች ግዢና የባንኩን የክፍያ ስዊች የማዘመን ስራ የተጠናቀቀ ሲሆን የሞባይል ባንኪንግ መተግበሪያን ለደንበኞች ምቹ የማድረግ ስራ በሂደት ላይ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም የባንኩን የተለያዩ መተግበሪያዎች፤ ሲስተሞችና መረጃ ካልታሰበ ጥቃት ለመከላከል የሚያስችሉ የሳይበር ደህንነቱን የመጠበቅና የመከላከል ስራ ቀዳሚ የትኩረት አቅጣጫዎች ሆነው ቀጥለዋል፡፡

በሌላ በኩል የዲጂታል ባንኪንግ አገልግሎቶቻችንን የሚጠቀሙ ደንበኞችን የመመልመሉ ስራ የባንኩን የዲጂታል አቅሞች ከማጠናከርና ተደራሽነቱን ከማስፋት ጋር መሳ ለመሳ ቀጥሏል፡፡ በዚህ መሰረት ለሞባይል ባንኪንግ አገልግሎት ያመለከቱ ደንበኞች ቁጥር ካለፈው ዓመት በእጥፍ አድጎ 1.28 ሚሊዮን የደረሰ ሲሆን ለካርድ እና ኢንተርኔት አገልግሎት ያመለከቱ ደንበኞች ቁጥር ድምር ወደ 685 ሺህ ተጠግቷል፡፡ በሌላ በኩል የነዚህ አገልግሎቶች ተጠቃሚ ደንበኞች ቁጥር በእጥፍ ከፍ ብሎ የሶስቱም አገልግሎቶች ተጠቃሚ ደንበኞች ብዛት በአጠቃላይ ከ1.1 ሚሊዮን በላይ ሆኗል፡፡

### 1.3.4 ማህበራዊ ኃላፊነት

ዓባይ ባንክ ከቅርንጫፍ ስርጭቱ በላቀ ሁኔታ ለማህበረሰቡ ይበልጥ ተደራሽ በመሆን ለማህበራዊ ደህንነት የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ በተጠናቀቀው ዓመትም ቀጥሎበታል፡፡ ባንኩ የገነባው ማህበረሰባዊ ሃላፊነትን የመወጣት ጠንካራ ባህል የማህበረሰቡን ዕሴቶች በማክበር ለሁሉም ባለድርሻዎች ፍትሃዊ ዕድሎችን በመፍጠር፣ በበጎ አድራጎት ስራዎች ላይ በመሳተፍ፣ የባንኩን አገልግሎቶች በሃላፊነት በመምራትና ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የማህበረሰብ አካላት ተገቢውን ድጋፍ በመስጠት ድርሻውን በአግባቡ በመወጣት ላይ ይገኛል፡፡

በመሆኑም በተጠናቀቀው ዓመት ለተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች፣ ለልማታዊ ተግባራት እና ለበጎ አድራጎት ስራዎች የሚውል የብር 34.6 ሚሊዮን ዋጋ ያላቸው የተለያዩ ድጋፎችን በማበርከት ከማህበረሰቡ ጋር ያለውን ቁርኝት ለማጠናከር ጥረት አድርጓል፡፡

### 1.3.5 ሪስክ ማኔጅመንት እና ኮምፕሊያንስ

የተሰማራንበት የባንክ ዘርፍ ለበርካታ ኢኮኖሚያዊና ሌሎች ስጋቶች በእጅጉ ተጋላጭ የሆነ በመሆኑ የተቆጣጣሪው አካል ጥብቅ ክትትል ይሻል፡፡ በመሆኑም ጠንካራ የስጋት አስተዳደር መዘርጋት ከኢንደስትሪው ዐብይ ተግባራት መካከል አንዱ ነው፡፡ ይህን ተከትሎም ባንኩ ጥብቅ የሪስክ ማኔጅመንት ስርዓት ተግባራዊ ያደረገ ሲሆን የሪስክና ኮምፕሊያንስ ዳሰሳዎችን በመደበኛነት በማከናወን የባንኩ የዕለት ተዕለት ተግባራት አካል እንዲሆኑና የዳበረ የስጋት ክትትል ባህል እንዲፈጠር በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑም የባንኩን ዋነኛ የስጋት ምንጮችን በመለየትና የስጋት ደረጃዎችን በመለካት ተገቢ ማስተካከያዎችን በመተግበር የስጋት ጫናውን ለመቀነስ ተሞክሯል፡፡

የሪስክ ማኔጅመንት ስርዓቱን ከማጠናከር አንጻር በርካታ ስራዎች የተሰሩ ሲሆን ከነኚህ መካከል የውስጥ ቁጥጥር ስርዓቱን በቅርበት መከታተል፣ የፖሊሲዎችና የመመሪያዎች ክለሳ ማከናወን እንዲሁም የስጋት ዳሰሳ ጥልቀትንና የትንተና መለኪያዎች የማጎልበት ስራ ተጠቃሾች ናቸው፡፡

## 1.3.6 የህንጻ ግንባታ ፕሮጀክቶች

የተጠናቀቀው ዓመት የኮንስትራክሽን ዘርፉንም ሆነ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶቻችንን አፈጻጸም የሚገድቡ በርካታ ተግዳሮቶች የታዩበት ዓመት ቢሆንም የባንካችን ዋነኛ ፕሮጀክቶች በአንጻራዊነት የተሻለ አፈጻጸም ተመዝግቦባቸዋል፡፡ በዚህም መሰረት የዋናው መስሪያ ቤት እና የደሴ ቅይጥ አገልግሎት ህንጻዎች ግንባታ የሱፐር ስትራክቸር ግንባታዎች በሂደት ላይ የሚገኙ ሲሆን የባህርዳር እና የጥቁር ዓባይ ፕሮጀክቶች የሰብስትራክቸር ስራዎች በመሰራት ላይ ይገኛሉ፡፡ ምንም አንኳን አካባቢያዊ ተለዋዋጭ ሁኔታዎች ሊገድቡን ቢችሉም የዋናው መስሪያ ቤት እና የደሴ ቅይጥ አገልግሎት ህንጻዎች የሱፐር ስትራክቸር ግንባታ በቀጣዩ ዓመት ለማጠናቀቅ ጥረት ይደረጋል፡፡

## 1.4 ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች

በቀጣዩ ዓመት የባንካችንን የጉዞ ከፍታ ራዕይ ለማሳካት የሚያስችሉ አዲስ በተዘጋጀው የአምስት ዓመት መሪ ዕቅድ የተቀመጡ ግቦችን ለማስፈጸም ትኩረት በመስጠት የመሪ ዕቅዱን ሁነኛ ትልሞች ለሁሉም የባንኩ አካላት በማስርጽ እና ዋነኛ የስትራቴጂ ማስፈጸሚያ ስልቶችን ለመተግበር የሚያስችል ሙሉ ቁመና ላይ መገኘት ቀዳሚ ትኩረታችን ነው፡፡

በዚህም መሰረት የባንኩን ስትራቴጂ ለማስፈጸም የሚያስችል ዝግጁነት ለመፍጠር የሰው ኃይል ብቃትን የማሳደግ እና የዲጂታል ቴክኖሎጂ አቅሞቻችንን የማጎልበት ስራዎች በስፋት ይከናወናሉ፡፡

ምንም እንኳ በሀገራችን የሚስተዋለው ተለዋዋጭ ከባቢያዊ ሁኔታዎች በትርፋማነታችን ላይ ሊፈጥሩት የሚችሉት ስጋት ከፍ ያለ ቢሆንም የወጪ ጫናዎችን ሊቀንሱ በሚችሉ ዘርፎቻችን ላይ በተለየ ትኩረት በመንቀሳቀስ ውጤታማ ስራ ለማበርከት ጥረት ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም በቀደሙት ዓመታት የተመዘገቡ ስኬቶችን በማስቀጠል የሃብት አሰባሰብ፣ የካፒታል ዕድገት፣ ተደራሽነት ማስፋት፣ የደንበኞቻችንን ቁጥር ማሳደግና የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶቻችንን በጥልቅ ዲሲፕሊን መከታተል ዓበይት ትኩረቶቻችን ሆነው ይቀጥላሉ፡፡ ይህንን ለማሳካትም የባንካችንን ተቋማዊ ልምዶች በጠንካራ ትጋት እንተገብራለን፡፡



ዓባይ - ታማኝ አገልጋይ !
**Abay : The Trustworthy Bank !**

# ክፍል 2

## የኦዲተሮች ሪፖርት



የዓባይ ባንክ ህንፃ ዲዛይን - ባህርዳር



የዓባይ ባንክ ህንፃ ዲዛይን - ደሴ

TMS Plus
Tafesse,Shisema and Ayalew Certified Audit Partnership
Chartered Certified Accountants (UK) and Authorised Auditors (Ethiopia)
HLB Ethiopia
Member Firm of HLB International
THE GLOBAL ADVISORY AND ACCOUNTING NETWORK
Tel. 251-011-8961752 /011 6180638 Mob. 0911 229425 /0930 034356/0930 034357 Fax: 251-011 662 12 70/60
E-mail:- tmsplus@ethionet.et / tafessef@hotmail.com P.O.Box 110690 Addis Ababa - Ethiopia

**የዓባይ ባንክ አክሲዮን ማህበር ለ2015 ዓ.ም የበጀት አመት በተዘጋጀው ሂሳብ ላይ የቀረበ**

**<u>የውጭ ኦዲተሮች ሪፖርት በሂሳብ መግለጫዎች ኦዲት ላይ የቀረበ ሪፖርት</u>**

**የሙያ አስተያየት**

ከዚህ ሪፖርት ጋር ተያይዘው የቀረቡትንና እ.አ.አ ጁን 30/ 2023 (በእኛ አቆጣጠር ሰኔ 23 ቀን 2015 ዓ.ም) ለተጠናቀቀው የበጀት ዓመት የተዘጋጁትን የዓባይ ባንክ አክሲዮን ማህበር የሀብትና ዕዳ መግለጫ፤ የትርፍና ኪሳራ እና ሌሎች ጠቅላላ ገቢዎች መግለጫ፤ በተጣራ ሃብት ላይ የታየ ለውጥ መግለጫ ፤ የጥሬ ገንዘብ ፍሰት መግለጫ እንዲሁም ኩባንያው የሚከተላቸውን የሂሳብ አሰራር ፖሊሲዎች እና ማብራሪያዎች ያካተቱትን የሂሳብ መግለጫዎች ኦዲት አድርገናል፡፡

በእኛ አስተያየት ከዚህ ሪፖርት ጋር ተያይዘው የቀረቡት የሂሳብ መግለጫዎችና አባሪዎቻቸው አለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎችን (IFRS) ተከትለው የተዘጋጁ ሲሆኑ በአጠቃላይ አክሲዮን ማህበሩ እ.አ.አ ጁን 30/ 2023 የነበረውን ሀብትና ዕዳ እንዲሁም በዚያው ዕለት ላለቀው ዓመት የነበረውን የሂሳብ እንቅስቃሴ እና የጥሬ ገንዘብ ፍሰት በሚገባ ያሳያሉ፡፡

**የአስተያየታችን መሰረት**

የኦዲት ስራችንን ያከናወንነው አለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን በመከተል ሲሆን በእነዚህ ደረጃዎች መሰረት የሚጠበቅብን ኃላፊነት ከዚህ በታች የኦዲተሮች ሃላፊነት በሚለው ርዕስ ስር ተመልክቷል፡፡ የአለም አቀፍ የሂሳብ ባለሙያዎች የስነምግባር ደረጃዎች ቦርድ ለሂሳብ ባለሙያዎች ያወጣው የስነ-ምግባር ኮድ በሚጠይቀው እና በኢትዮጵያ ውስጥ ለተካሄደው ኦዲት አስፈላጊ በሆኑት የስነምግባር መርሆዎች መሰረት ከአክሲዮን ማህበሩ ነጻ እና ገለልተኛ ሆነን ስራችንን አከናውነናል፡፡ እንዲሁም የስነምግባር ደንቡ የሚጠይቃቸውን እና የሚጠበቁብንን ሌሎች ኃላፊነቶች አሟልተናል፡፡

ከዚህ በላይ የሰጠነው የሙያ አስተያየት ደረጃውን ተከትለን ባከናወንነው የኦዲት ስራና በቀረበልን የኦዲት ማስረጃ በመተማመን ነው፡፡

**ቁልፍ የኦዲት ጉዳዮች**

ቁልፍ የኦዲት ጉዳዮች የሚባሉት በእኛ ሙያዊ ግምት በአመቱ የሂሳብ መግለጫዎች ኦዲት ወቅት ከፍተኛ ትኩረት የተሰጣቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡ እነዚህ ጉዳዮች በሂሳብ መግለጫዎች ኦዲት እና በዚሁ መነሻነት የሙያ አስተያየት ለመስጠት አጠቃላይ ትኩረት የተሰጣቸው ቢሆኑም በነዚህ ጉዳዮች ላይ የተናጠል አስተያየት አልሰጠንም ፡፡

በሂሳብ ማብራሪያዎች ተራ ቁጥር 11 እና 12 እንደተገለፀው የብድር መጠባበቂያ ወጪ /ኢምፔይርመንት ሎስ/አለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃ ቁጥር 9 (IFRS 9) (ፋይናንሻል ኢንስትሩመንት) መሰረት አድርጎ የተወሰነ ነው፡፡ ይህ ቁልፍ የኦዲት ጉዳይ ተደርጎ የተወሰደበት ምክንያት አለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃ ቁጥር 9 (IFRS 9)(ፋይናንሻል ኢንስትሩመንት) የመጠባበቂያ ወጪን ለመወሰን መሰረታዊ የግምት ስራ የሚጠይቀው ውስብስብ ደረጃ በመሆኑ ነው ፡፡

**የኦዲት አሰራር ስርዓት**

የብድር መጠባበቂያ ወጪ /ኢምፔይርመንት ሎስ/በአለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃ ቁጥር 9 (IFRS 9) (ፋይናንሻል ኢንስትሩመንት) መሰረት አድርጎ የተሰላ መሆኑን ለማረጋገጥ የታሳቢዎቹን አግባብነት ለመገምገም የሚያስችል የኦዲት አሰራር ስርዓት ተከትለናል ፡፡

አለም አቀፍ የሂሳብ ሪፖርት ደረጃ 13 (ፌር ቫልዩ ግምታ) ተቋሞች በተቻለ መጠን የሚታዩ ግብአቶችን በመጠቀም እነዚህ የሚታዩ ግብአቶች በማይገኙበት ሁኔታ ደግሞ የማይታዩ ግብአቶችን በመጠቀም ፌር ቫልዩ እንዲገምቱ ይጠቅማል፡፡

ባንኩ በሌሎች ተቋሞች ያለውን ኢንቨስትመንት ፌር ቫልዩ ለመገመት የሚታዩ ግብአቶች የሌሉ በመሆኑ የማይታዩ ግብአቶችን የሚጠቅም እንደ ዲስካውንት ሬት እና የወደፊት የጥሬ ገንዘብ  ፍሰት የመሳሰሉት የግመታ ሞዴል በመጠቀም ግመታውን አከናውኗል።

የማይታዩ ግብአቶችን የሚጠቀም ሞዴል እንደገማቹ እይታ ሊለያይ ስለሚችል በሂሣብ መግለጫዎች ላይ ጉልህ ስህተት ሊያሳድር ይችላል የሚል ስጋት ይፈጥራል፡፤

ይህ ቁልፍ ጉዳይ ተደርጎ የተወሰደበት በሚከተሉት ሁኔታዎች ምክንያት ነው።

- ባንኩ በሌሎች ተቋሞች ያለው ኢንቨስትመንት ለሂሣብ መግለጫዎች ጉልህ ነው፡፤
- ግመታው ውስብስብ እና የተለያዩ የማይታዩ ግብአቶች መጠቀምን ይጠይቃል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ የሚከተሉትን የኦዲት ተግባሮች አከናውነናል።

- የባንኩን ግመታ ዘዴ ግምገማ በማድረግ የተወሰዱት ቁልፍ ታሳቢዋች ምክንያታዊ መሆናቸውን መርምረናል።
- የባንኩን የግመታ ውጤት ከነጻ ገበያ ተሳታፊዎች ጋር አነፃፅረናል።

ከኦዲት ሂደት ውጤት በመነሳት ባንኩ በሌሎች ተቋሞች ያለው ኢንቨስትመንት ግመታ ምክንያታዊ እና አለም አቀፍ የሂሳብ ሪፖርት ደረጃ 13 የሚጠይቀውን ያሟላ ነው የሚል እምነት አለን። ይሁንና ባንኩ ለወደፊት ሊኖር የሚችለውን ጉልህ ስህተት ለመቀነስ የሚከተሉትን እርምጃዋች እንዲወስድ እንመክራለን።

- በአብዛኛው ሊታዩ የሚችሉ ግብአቶን የሚያካትት የግመታ ዘዴ እንዲጠቀም
- በየጊዜው የኢንቨስትመንቶቹን አፈፃፀም እየተከታተለ የግመታ ሞዴሉን እንዲያሻሽል

በተጨማሪም በሒሳብ መግለጫ ተራ ቁጥር 38 ላይ እንደተገለጸው ለኮንስትራክሽን ኩባንያዎች የተሰጠው የሥራ አፈጻጸምና የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና እንደ ውሉ እንዲፈፀም ባንኩ በዚህ ጉዳይ ላይ ጥብቅ ክትትልና እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል።

**የሂሳብ መግለጫዎችን በተመለከተ የዳሬክተሮች ቦርድ ኃላፊነት**

አለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎችን በመከተል የሂሳብ መግለጫዎችን አዘጋጅቶ ማቅረብ እንዲሁም ሆን ተብሎም ሆነ ወይንም በስህተት ከሚፈፀም ጉልህ ስህተት ነፃ የሆኑ የሂሳብ መግለጫዎችን ለማዘጋጀት አስፈላጊ ናቸው ብሎ ያመነባቸውን የውስጥ ቁጥጥር ስርዓቶች መዘርጋት የባንኩ የዳሬክተሮች ቦርድ ኃላፊነት ነው። ቦርዱ የሂሳብ መግለጫዎችን በሚያዘጋጅበት ወቅት የኩባንያውን ቀጣይነት በመገምገም ስጋት የሚፈጥሩ ሁኔታዎችን በግልፅ ማመላከትና የኩባንያውን መፍረስ ወይም የአንዳንድ ኦፐሬሽኖችን ስራ ማቆም የሚያስገድዱ ሁኔታዎች ካላጋጠሙ በስተቀር የኩባንያውን ቀጣይነት በማሰብ ሂሳቡ የተዘጋጀ መሆኑን የመግለፅ ኃላፊነት አለበት።

የዳይሬክተሮች ቦርድ የኩባንያውን የፋይናንሻል ሪፖርት ሂደት የመከታተል ተጨማሪ ኃላፊነት አለበት ።

**የኦዲተሮች ኃላፊነት**

የእኛ ኃላፊነት የቀረቡት የሂሳብ መግለጫዎች ሆን ተብሎም ሆነ በስህተት ከሚፈፀም ጉልህ ስህተት ነፃ ስለመሆናቸው ምክንያታዊ ማረጋገጫ መስጠትና ይህንኑ አስተያየታችንን በሪፖርታችን መግለፅ ነው። ምክንያታዊ የሆነ ማረጋገጫ ለመስጠት የሚከናወነው ተግባር በሂሳቡ ውስጥ ሊኖሩ የሚችሉ ጉልህ ስህተቶችን በሙሉ ፈልጎ ያገኛል ተብሎ አይጠበቅም። ምክንያቱም ምክንያታዊ ማረጋገጫ በከፍተኛ ደረጃ የሚታይ የማረጋገጥ ሂደት በመሆኑ አለም አቀፍ የኦዲት ደረዳዎችን በመከተል የሚከናወነው ኦዲትም ቢሆን ጉልህ ስህተቶችን ሁልጊዜ ፈልጎ የማግኘት ዋስትና ስለማይሰጥ ነው። ስህተቶች ሆን ተብሎ ወይንም በስህተት የሚፈጸሙና በተናጠል ወይም በድምር ጉልህ ሆነው የሂሳብ መግለጫዎችን መሰረት አድርጎ በሚወሰን ኢኮኖሚያዊ ውሳኔ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ።

**የሌሎች ህጋዊ ሁኔታዎች ኦዲት ሪፖርት**

በ 2013 ዓ.ም በወጣው የኢትዮጵያ ንግድ ህግ አዋጅ 1243/2021 በሚያዘው መሰረት የቀረበው የዳሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት ላይ የሂሳብ መግለጫዎቹን በተመለከተ ከቀረበው ሪፖርት የተለየ አስተያየት የሌለን መሆኑን እየገለጽን ጠቅላላ ጉባኤው የዳሬክተሮቹን ሪፖርት እንዲያፀድቀው አስተያየታችንን እንሰጣለን።

ከዚህ በተጨማሪ የዳይሬክተሮች ቦርድ የትርፍ ክፍፍል ሃሳብ ስለማድረጉ ማስረጃ ስላልቀረበልን በንግድ ህጉ በሚያዘው መሠረት አስተያየት አልሰጠንም።

**ታፈሰ፣ ሺሰማ እና አያሌው የኦዲት አገልግሎት የህብረት ሽርክና ማኅበር**
**የተመሰከረላቸው የሂሳብ አዋቂዎች(ዩኬ)**
**የተፈቀደላቸው ኦዲተሮች (ኢትዮጵያ) አዲስ አበባ**
**የአባይ ባንክ አክስዮን ማህበር የውጭ ኦዲተሮች**
**መስከረም 26 ቀን 2016 ዓ.ም**

## ዓባይ ባንክ አክሲዮን ማህበር
## እ.ኤ.አ በሰኔ 30 ቀን 2023 ለተጠናቀቀው የሂሳብ ዓመት
## የትርፍ ወይም ኪሳራ እና ሌሎች አጠቃላይ ገቢዎች መግለጫ

| | ማብራሪያ | ሰኔ 30 2023 ብር'000 | ሰኔ 30 2022 ብር'000 |
|---|---|---|---|
| የወለድ ገቢ | 5 | 5,547,522 | 3,543,341 |
| የወለድ ወጪ | 6 | (1,569,189) | (1,126,413) |
| **የተጣራ የወለድ ገቢ** | | **3,978,333** | **2,416,928** |
| የኮሚሽንና አገልግሎት ገቢ | 7 | 1,241,979 | 640,140 |
| የኮሚሽንና አገልግሎት ወጪ | 8 | (54,407) | (17,650) |
| **የተጣራ ኮሚሽንና የአገልግሎት ገቢ** | | **1,187,572** | **622,490** |
| የተጣራ የዉጭ ምንዛሪ ገቢ | 9 | 154,927 | 112,972 |
| ከሌላ የመደበኛ ሥራ የተገኘ ገቢ | 10 | 57,383 | 36,107 |
| | | **212,310** | **149,079** |
| **አጠቃላይ የመደበኛ ሥራ ገቢ** | | **5,378,215** | **3,188,497** |
| ለብድር የተያዘ መጠባበቂያ | 11 | (207,867) | (92,175) |
| ለሌሎች ሀብቶች የተያዘ መጠባበቂያ | 12 | (11,444) | (6,978) |
| **የተጣራ የመደበኛ ሥራ ገቢ** | | **5,158,904** | **3,089,344** |
| የሰራተኛ ወጭዎች | 13 | (1,966,996) | (1,094,626) |
| የእርጅና ተቀናሽ | 23-24 | (121,535) | (87,281) |
| የሊዝ ሀብት የእርጅና ተቀናሽ | 21 | (180,979) | (133,241) |
| የሊዝ ዕዳ ወለድ ተከፋይ ወጪ | 22 | (10,241) | (23,281) |
| ለሌላ የመደበኛ ሥራ የወጣ ወጪ | 14 | (754,737) | (450,002) |
| **ከትርፍ ግብር በፊት የተገኘ ትርፍ** | | **2,124,416** | **1,300,913** |
| የትርፍ ግብር | 15 | (572,945) | (367,648) |
| **ከትርፍ ግብር በኋላ የተገኘ ትርፍ** | | **1,551,471** | **933,265** |
| **በትርፍና ኪሳራ መዝገብ የማይካተቱ ገቢዎች/ወጪዎች/** | | | |
| ከሰራተኞች የአገልግሎት ጥቅማጥቅም ዳግም ልኬት ገቢ(ወጪ) | 30 | (36,051) | (4,085) |
| በወቅታዊ የአክስዮን ኢንቨስትመንት ግምት የመጣ ገቢ/ወጪ | 18 | 199,016 | 116,911 |
| የረጅም ጊዜ የግብር ዕዳ ወጭ ስሌት ማስተካከያ | 15 | (10,815) | (1,226) |
| | | 152,150 | 111,601 |
| **ከታክስ በኋላ ያሉ የተጣሩ ሌሎች አጠቃላይ የአመቱ የስሌት ገቢዎች** | | **1,703,621** | **1,044,866** |
| **እያንዳንዱ አክሲዮን ያስገኘዉ ትርፍ (የአንዱ ዋጋ 1,000)** | 32 | **360.03** | **295.08** |

ከገጽ 10 - 34 ያሉት ማብራሪያዎች የሪፖርቱ ዋነኛ አካል ናቸው።

# ዓባይ ባንክ አክሲዮን ማህበር
# እ.ኤ.አ በሰኔ 30 ቀን 2023 ላይ የታየ
# የሃብትና የዕዳ ሂሳብ መግለጫ

| | ማብራሪያ | ሰኔ 30 2023 ብር ('000) | ሰኔ 30 2022 ብር ('000) |
|---|---|---|---|
| **ሀብት** | | | |
| በእጅና በባንክ የሚገኝ ጥሬ ገንዘብ | 16 | 8,247,918 | 7,920,786 |
| ለደንበኞች የተሰጠ ብድርና ቅድሚያ ክፍያ(የተጣራ) | 17 | 36,474,351 | 26,594,569 |
| የአክሲዮን ኢንቨስትመንት | 18 | 505,679 | 298,728 |
| ሌሎች ፋይናንሺያል ሀብቶች | 19 | 5,667,844 | 3,182,409 |
| ፋይናንሺያል ያልሆኑ ሀብቶች | 20 | 705,778 | 941,906 |
| የሊዝ መብት | 21 | 927,495 | 639,439 |
| ቋሚ ንብረቶች (የተጣራ) | 23 | 1,141,539 | 575,235 |
| ግዙፋዊ ሀልዎት የሌላቸው ሃብቶች | 24 | 19,582 | 27,032 |
| በሂደት ላይ ያለ የህንፃ ግንባታ ሥራ | 25 | 1,359,729 | 501,634 |
| ሊሸጡ በመያዣ የተያዙ ንብረቶች | 26 | 7,351 | 13,758 |
| ወደፊት የሚሰበሰብ ሀብት | 15 | 850 | - |
| **ጠቅላላ ሀብት** | | **55,058,113** | **40,695,496** |
| **ዕዳዎች** | | | |
| የደንበኞች ተቀማጭ ገንዘብ | 27 | 41,769,515 | 32,397,350 |
| የዓመቱ ተከፋይ የትርፍ ግብር | 15 | 572,945 | 367,648 |
| ፋይናንሺያል ዕዳ | 28 | 4,364,775 | 1,571,928 |
| የሊዝ ተከፋይ ዕዳ | 22 | 507,520 | 391,992 |
| ፋይናንሺያል ያልሆነ ዕዳ | 29 | 53,257 | 44,154 |
| የሰራተኞች ጥቅማጥቅም ዕዳ | 30 | 119,001 | 65,219 |
| ወደፊት የሚከፈል የግብር ዕዳ | 15 | 0 | 610 |
| **ጠቅላላ ዕዳዎች** | | **47,387,013** | **34,838,901** |
| **ካፒታልና መጠባበቂያ ሒሳቦች** | | | |
| የተከፈለ ካፒታል | 31 | 4,733,303 | 3,971,031 |
| ሼር ኘሪምየም | 31 | 35,388 | 35,208 |
| ያልተከፋፈለ ትርፍ | 33 | 1,041,760 | 658,748 |
| የሰራተኛ የአገልግሎት ጥቅማጥቅም መጠባበቂያ | 30 | (61,611) | (25,560) |
| ከአክስዮን ኢንቨስትመንት መጠባበቅያ ሂሳብ | 18 | 370,768 | 171,751 |
| ሕጋዊ የመጠባበቂያ ሂሳብ | 34 | 1,308,302 | 920,434 |
| በብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሰረት ለብድርና ተሰብሳቢዎት የተያዘ ተጨማሪ መጠባበቂያ | 35 | 243,190 | 124,983 |
| **ጠቅላላ ካፒታልና መጠባበቂያ ሒሳቦች** | | **7,671,100** | **5,856,595** |
| **ጠቅላላ ዕዳ፤ ካፒታልና መጠባበቂያ ሒሳቦች** | | **55,058,113** | **40,695,496** |

ከገጽ 10 - 34 ያሉት ማብራሪያዎች የሪፖርቱ ዋነኛ አካል ናቸው፡፡

የኩባንያው አስተዳዳሪዎች ከገጽ 10 - 34 ያሉት የሂሳብ መግለጫዎች በቀረቡበት መልኩ እንዲወጡ እ.ኤ.አ ኦክቶበር 07 2023 ፈቅደው አፅድቀዋል፡፡

ዶ/ር አምላኩ አስረስ______________
የቦርድ ሰብሳቢ

የኋላ ገሠሠ______________
ዋና ሥራ አስፈጻሚ

# ዓባይ ባንክ አክሲዮን ማህበር
# እ.ኤ.አ በሰኔ 30 ቀን 2023 ለተጠናቀቀው የሂሳብ ዓመት
# በአክሲዮን ማህበሩ ካፒታል ላይ የታየውን ለውጥ የሚያሳይ መግለጫ

| | ማብራሪያ | የተከፈለ ካፒታል ብር '000 | ሼር ፕሪምየም ብር '000 | ያልተከፋፈለ ትርፍ ብር '000 | ሌሎች መጠባበቂያ ብር '000 | ሕጋዊ መጠባበቂያ ብር '000 | አጠቃላይ መጠባበቂያ ብር '000 | ከአክስዮን ኢንቨስትመንት ብር '000 | ድምር ብር '000 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **እ.ኤ.አ በሀምሌ 1 ቀን 2021 የታየ** | | **2,812,741** | **28,365** | **600,916** | **1,364** | **687,116** | **65,438** | **32,001** | **4,227,941** |
| ከአዲስ አክሲዮኖች ሽያጭ የተከፈለ | 31 | 1,158,290 | 6,843 | - | - | - | - | - | 1,165,133 |
| በአመቱ የተገኘ ትርፍ | 32 | - | - | 933,265 | - | - | - | - | 933,265 |
| የተከፋፈለ የትርፍ ድርሻ | 33 | - | - | (548,685) | - | - | - | - | (548,685) |
| የዳይሬክተሮች የትርፍ ድርሻ | 33 | - | - | (1,350) | - | - | - | - | (1,350) |
| ከሰራተኞች የአገልግሎት ጥቅማጥቅም ዳግም ልኬት ገቢ(ወጪ) | 30 | - | - | - | (4,085) | - | - | - | (4,085) |
| የአክስዮን ኢንቨስትመንት ወቅታዊ ግምት | 18 | - | - | - | - | - | - | 116,911 | 116,911 |
| ወደ ሌሎች መጠባበቂያ የዞረ | 35 | - | - | (59,545) | - | - | 59,545 | - | - |
| የዘገየ የግብር እዳ | 33 | - | - | 18,843 | - | - | - | - | 18,843 |
| ወደ ህጋዊ መጠባበቂያ የዞረ | 34 | - | - | (233,318) | - | 233,318 | - | - | - |
| የቅድመ ጊዜ ማስተካከያ | 33 | - | - | (51,378) | (22,839) | - | - | 22,839 | (51,378) |
| **እ.ኤ.አ በሰኔ 30 ቀን 2022 ላይ የታየ** | | **3,971,031** | **35,208** | **658,748** | **(25,560)** | **920,434** | **124,983** | **171,751** | **5,856,594** |
| **ጠቅላላ ካፒታልና መጠባበቂያ ሒሳቦች** | | | | | | | | | |
| **እ.ኤ.አ በሀምሌ 1 ቀን 2022 የታየ** | | **3,971,031** | **35,208** | **658,748** | **(25,560)** | **920,434** | **124,983** | **171,751** | **5,856,594** |
| | | - | - | - | - | - | - | - | - |
| ከአዲስ አክሲዮኖች ሽያጭ የተከፈለ | 31 | 762,272 | 180 | - | - | - | - | - | 762,452 |
| በአመቱ የተገኘ ትርፍ | 32 | - | - | 1,551,471 | - | - | - | - | 1,551,471 |
| የተከፋፈለ የትርፍ ድርሻ | 33 | - | - | (658,748) | - | - | - | - | (658,748) |
| የዳይሬክተሮች የትርፍ ድርሻ | 33 | - | - | (1,350) | - | - | - | - | (1,350) |
| ከሰራተኞች የአገልግሎት ጥቅማጥቅም ዳግም ልኬት ገቢ(ወጪ) | 30 | - | - | - | (36,051) | - | - | - | (36,051) |
| የአክስዮን ኢንቨስትመንት ወቅታዊ ግምት | 18 | - | - | - | - | - | - | 199,016 | 199,016 |
| ወደ ሌሎች መጠባበቂያ የዞረ | 35 | - | - | (118,207) | - | - | 118,207 | - | - |
| የዘገየ የግብር እዳ | 33 | - | - | 1,459 | - | - | - | - | 1,459 |
| ወደ ህጋዊ መጠባበቂያ የዞረ | 34 | - | - | (387,868) | - | 387,868 | - | - | - |
| የቅድመ ጊዜ ማስተካከያ (IFRS) | 33 | - | - | (3,745) | - | - | - | - | (3,745) |
| **እ.ኤ.አ በሰኔ 30 ቀን 2023 ላይ የታየ** | | **4,733,303** | **35,388** | **1,041,760** | **(61,611)** | **1,308,301** | **243,190** | **370,767** | **7,671,099** |

**ጠቅላላ ካፒታልና መጠባበቂያ ሒሳቦች**

ከገጽ 10 - 34 ያሉት ማብራሪያዎች የሪፖርቱ ዋነኛ አካል ናቸው፡፡

# ዓባይ ባንክ አክሲዮን ማህበር
# እ.ኤ.አ በሰኔ 30 ቀን 2023 ለተጠናቀቀው የሂሳብ ዓመት
# የጥሬ ገንዘብ ፍሰት መግለጫ

| | ማብራሪያ | ሰኔ 30 2023 ብር '000 | ሰኔ 30 2022 ብር '000 |
|---|---|---|---|
| **ከመደበኛ ሥራ እንቅስቃሴ የተገኘ የተጣራ ገንዘብ** | | | |
| ከመደበኛ ሥራ እንቅስቃሴ የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ፍሰት | 36 | 4,207,523 | 2,196,388 |
| ለትርፍ ግብር የተከፈለ | 15 | (367,648) | (305,743) |
| የዘገየ የግብር እዳ /ተመላሽ/ | | (3,745) | (52,230) |
| **ከመደበኛ ሥራ እንቅስቃሴ የተገኘ የተጣራ ገንዘብ ገቢ** | | **3,836,130** | **1,838,414** |
| **ለኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ የወጣ** | | | |
| የኢንቨስትመንት ጭማሪ ግዢ | 19 a | (2,063,927) | 942,653 |
| የአክሲዮን ግዢ ኢንቨስትመንት | 18 | (7,934) | (5,000) |
| ለሊዝ የተከፈለ | 25 | (858,095) | (172,221) |
| ግዙፋዊ ህልዎት ለሌላቸው ሃብቶች ተከፈለ | 24 | - | - |
| የቋሚ ዕቃዎች ግዢ | 23 | (681,873) | (101,751) |
| ከቋሚ ዕቃዎች ሽያጭ የተገኘ ገቢ | 36 | 476 | 2,042 |
| **ከኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ የተገኘ የተጣራ ወጪ** | | **(3,611,353)** | **665,723** |
| **ከፋይናንሲንግ እንቅስቃሴ** | | | |
| የትርፍ ድርሻ ተከፈለ | 33 | (658,748) | (548,685) |
| ተጨማሪ የተሸጡ አክሲዮኖች | 31 | 762,452 | 1,165,133 |
| ለዳይሬክተሮች ቦርድ የትርፍ ድርሻ የተከፈለ | 33 | (1,350) | (1,350) |
| **ከፋይናንሲንግ እንቅስቃሴ የተገኘ የተጣራ ገንዘብ** | | **102,354** | **615,098** |
| **የዓመቱ የተጣራ የጥሬ ገንዘብ ጭማሪ** | | **327,132** | **3,119,235** |
| በአመቱ መጀመሪያ ላይ የነበረ የገንዘብ መጠን | 16 | 7,920,786 | 4,801,551 |
| የዓመቱ የተጣራ የጥሬ ገንዘብ ጭማሪ/ቅናሽ | 16 | 327,132 | 3,119,235 |
| **በአመቱ መጨረሻ ላይ የታየ የገንዘብ መጠን** | 16 | **8,247,918** | **7,920,786** |

ከገጽ 10 - 34 ያሉት ማብራሪያዎች የሪፖርቱ ዋነኛ አካል ናቸው፡፡